# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፣ቁጥር ፪፣መስከርም ፳፻፲፫ ዓ.ም

**ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ** በሚል ርዕስ በየሁለት ወሩ በአካባቢ፣ ደንና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እየተዘጋጀች የምትሰራጨው ይህቺ ዜና መፅሄት የኢትዮጵያን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ለመቀነስ የተዘጋጀውን ዕቅድና አፈፃፀሙን በተመለከተ መረጃዎችንና አዳዲስ እውቀቶችን ለተለያዩ ባለድርሻዎች የማድረስ ዓላማ አላት፡፡



"ተስማምተንና ተግባብተን ያለንን አቅም አሰባስበን በጋራ ፍላጎታችን ላይ ስንዘምት ምን ማድረግ እንደምንችል [ይህ] ሕያው ምስክር ነው፡፡"

ክብርት ፕሬዘዳንት ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ

## በዚህ እትም. . .


አረንጓዴ አሻራ:- የኢትዮጵያ የአረንጓዴና የደን ልማት ስልታዊ ድጋፍ ፪

ዜናዎች ፪

ትኩረት ለፆታ ተኮር የአየር ንብረት እንቅስቃሴ ፫

ሁነቶች ፫

ልዩ ልዩ ህትመቶች ፮





**ዋና አዘጋጅ፥** ንጉሱ ለማ ገብሬ

**አዘጋጆች፥** ተስፋዬ ጋሻው፣ ሙሉነህ ገ/ሄደቶ እና ሮቢ ረዳ

**አምደኞች፥** መንሱር ደሴ እና መሀመድ አንዶሼ

**ግራፊክስና ሌይአውት፥** አርሴማ አንዳርጋቸው

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፣ቁጥር ፪

## ዜናዎች

### አዲስ አበባን ወደ አረንጓዴ ከተማነት መቀየር

የኢፌዲሪ ፕሬዘዳንት ክብርት ወ/ሮ ሳህለ ወርቅ ዘውዴና ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐብይ አህመድ እንዲሁም በርካታ የመንግስት የስራ ሀላፊዎች፤ የልማት አጋሮችና ከተለያዩ የማህበረሰብ ክፍሎች የተወከሉ አካላት በተገኙበት የሸገር ፓርክ የወንድማማች አደባባይ መስከረም 17 ቀን 2013 ዓ.ም በይፋ ተመርቆ ተከፍቷል። ፓርኩም በሀገራዊ የአረንጓዴ አሻራ ማዕቀፍ ውስጥ የተቀረፀና ኢትዮጵያ ለአረንጓዴ ልማት መሳካት ያላትን ቁርጠኝነት ያመላክታል፡፡ ምንጭ

### የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ልማት ጥሪ

75ኛውን የ.ተ.መ.ድ አመታዊ ጉባኤ በማስመልከት የኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ክቡር ዶ/ር ዐቢይ አህመድ በበይነ መረብ ለዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ባሰሙት ንግግር የኢትዮጵያን ተሞክሮና ቁርጠኛነት ዋቢ በመግለፅ "ዓለማቀፉ ማህበረሰብ ኮሮናን ጨምሮ የተጋረጡብንን በርካታ ተግዳሮቶች በዘላቂነት መቋቋም በሚያስችል መልኩ መፍታትና ማገገም ይኖርብናል" ብለዋል፡፡ በተጨማሪም “የኛ ትልምና ጥረት ከኮሮና ቫይረስ ሰቆቃ ወጥተን የተሻለ ነገን ማለም ብቻ ሳይሆን ወረርሽኙና ተያያዥ የአየር ንብረት ለውጥ ጠባይ የወለዳቸውን መሰናክሎች በዘላቂነት መቋቋም በሚያስችል ሁኔታ እንዲሆን በርትተን መስራት ነው” ብለዋል፡፡

ከወትሮው በተለየ አፅንኦት የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን በመከላከልና በመቋቋም ጥረቶች ላይ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ እንዲረባረብ አበክረው የገለፁት ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለው እንዳሉት "የአየር ንብረት ለውጥ እያስከተለ ያለውን ጥፋትና መዘዙን ለመረዳት በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በየዕለቱ ከምናስተውላቸው ቀውሶች የተሻለ ማስረጃ የለም" ብለዋል። ምንጭ

በተመሳሳይ ዜና የዓለማቀፉ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ማጣጣም ማዕከል የአፍሪካ ቢሮ በበይነ መረብ ለአባል ሀገራቱ ባዘጋጀው ውይይት ላይ በመሳተፍ ንግግር ያደረጉት የኢፌዲሪ ፕሬዘዳንት ክብርት ወ/ሮ ሳህለወርቅ ዘውዴ በአፅንኦት እንደገለፁት "የአፍሪካ ሀገራት ከኮሮና ቫይረስ ወረርሽኝ ባልተናነሰ የየሀገራቸውን የልማት ፖሊሲዎች የአየር ንብረት ለውጥን ተፅዕኖ ለመቋቋም በሚያስችል አግባብ መቃኘት ይገባል" ብለዋል፡፡ ክብርት ፕሬዘዳንቷ አክለውም ሀገራት በፓሪሱ የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ የተደረሰውን ስምምነት ለማሳካት ድርሻቸውን በቁርጠኛነት እንዲተገብሩ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ ምንጭ

## አረንጓዴ አሻራ:- የኢትዮጵያ የአረንጓዴና የደን ልማት ስልታዊ ድጋፍ

- በዶ/ር ተፈራ መንግስቱ፣ ብሄራዊ የአረንጓዴ ልማትና ችግኝ ተከላ አስተባባሪ ግብረ ኋይል ሰብሳቢ

ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት የሀገራችንን የበካይ ጋሶች ልቀት እ.አ.አ. በ2030 በ50% ለመቀነስ በምሰሶነት ከለያቸው ዘርፎች አንዱና ዋነኛው የደን ልማትና ጥበቃ ነው። ይህንን የዘርፉን የአረንጓዴ ልማት ርዕይ ለማሳካት መንግስት ቀርፆ በመተግበር ላይ ከሚገኛቸው ፕሮግራሞች መካከል አንዱ "ሬድ ፕላስ" በሚል የሚታወቀውና የደን ጭፍጨፋንና የመሬት መራቆትን በመታደግ ከደን ዘርፍ ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቀውን የበካይ ጋሶች ልቀት ለመቀነስ ታስቦ የተቀረፀ ስትራተጂካዊ እርምጃ ነው፡፡ ከዚህ ፕሮግራም ትግበራ ጎን ለጎንም "ሀገራዊ የደን ዘርፍ ሽግግር ፕሮግራም” በሚል የተቀረፀውና ለቀጣይ አስር አመታት የሚተገበረው የዘርፉ ዕቅድ፣ ሀገራዊ የጥቅል ሀብት ክምችትን ለማሳደግ፤ ተጨማሪ የስራ ዕድልን በዘርፉ ለመፍጠርና የበካይ ጋዞችን ልቀት መቀነስን ጨምሮ በርካታ አካባቢያዊና ስነምዳራዊ ፋይዳዎች አሉት፡፡ ይህም በመሆኑ የደን ልማት ከራሱ አልፎ በሌሎች ዘርፎች ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቁ በካይ ጋዞችን በመምጠጥ ቁልፍ ሚናን እንዲጫወት ሆኖ በሀገራችን የአረንጓዴ ልማት ስልት ውስጥ ተቀርፆል፡፡

በ2011 ዓ.ም ኢትዮጵያ "አረንጓዴ አሻራ" በሚል ስያሜ መሪነት በመላ ሀገሪቷ የሚተገበርና መልዐተ ህዝቡን ያሳተፈ የአረንጓዴ ልማትና ችግኝ ተከላ መርሀ ግብርን በማወጅ በክረምቱ ወራት የ4ቢሊዮን ችግኞችን እንዲሁም በአንድ ጀምበር 200 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል አቅዳ ተንቀሳቅሳለች። በዚህ ሀገራዊ የአረንጓዴ ልማት ዘመቻም 23 ሚሊዮን ዜጎችን ማሳተፍ የተቻለ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 30% (2.9 ሚሊዮኑ) አዋቂ እና ህጻናት ሴቶች ናቸው። በዚህ እንቅስቃሴም ከእቅዱ በላይ ማሳካት የተቻለ ሲሆን 4.75 ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል። ከዚህም ውስጥ 2.45 ቢሊዮን የዛፍ ችግኞች ሲሆኑ 2.3 ቢሊዮን ችግኞች ደግሞ የጥምር ግብርና ችግኝ ዝርያዎች ናቸው። ከዚህም ውስጥ 354 ሚሊዮን ችግኞችን በአንድ ጀምበር በሀምሌ 22/2011 ዓ.ም በመትከል የዘርፉን የዓለም ሪከርድ መያዝ ተችሏል።

የክረምቱን የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ተከትሎ ባሉ ጊዜያት የድሬ ተከላ እንክብካቤ ማለትም በደረቅ ወራት ውሀ የማጠጣት፣ የማረም፣ የመኮትኮትና በሞቱ ችግኞች ፋንታ ሌሎችን የመተካት ስራዎችን በማከናወን የችግኞቹን የፅድቀት መጠን ማሻሻል ተችሏል። በዚህም ክትትል በከሰሙ ችግኞች ፋንታ 13 ሚሊዮን ችግኞች ተተክተዋል፤ 3.2 ቢሊዮን ችግኞችንም በማረምና ውሀ በማጠጣት እድገታቸውን መጠበቅ ተችሏል። ይህንኑ የጥበቃና እንክብካቤ ስራ ውጤት ለማረጋገጥ በቅርቡ በተከናወነ ዳሰሳ የተተከሉ ችግኞች የፅድቀት መጠን 78% መሆኑ ተረጋግጧል። በ2011 ዓ.ም ተከላ የተካሄደባቸው ስፍራዎች በመሬት ላይ ስለመኖራቸው ለማረጋገጥ አመቺና ተደራሽም ናቸው። እንደ ማሣያም በአማራ ብሄራዊ ክልል 435 በመሬት ላይ የተለዩ የተከላ ስፍራዎች በግልፅ ተለይተው ክትትል እየተደረገ ይገኛል።

የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ልማትና ችግኝ ተከላ ብሄራዊ መርሀ ግብር በርካታ የልማት ስራዎችን በተቀናጀ መንገድ ምላሽ እንዲሰጥ ተደርጎ የተቀረፀና ፋይዳውም ዘርፈ ብዙ የሆነ ስትራጂካዊ እርምጃ ነው። ለዚህም ዓላማ መሳካት በማሰብ ጥምር ግብርና፣ የደን

**ከገፅ ፪ የቀጠለ...**

ዘርፍ ዘላቂ ልማት፣ አረንጓዴ ከተሞችን የመፍጠርና መልሶ ማደስ እንዲሁም የተቀናጀ የውሀና የአፈር ሀብት ጥበቃ በስትራተጂው እንዲካተቱ ተደርጓል። ይህ መሆኑ የሀገሪቱን ቀጣይና የረጅም ጊዜ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የአካባቢ ልማት ግቦችን ለማሳካት ይጠቅማል። ከዚህ ፋይዳ በተጨማሪም ሀገራችን የተቀበለቻቸውና የህጎቻችን አካል ያደረገቻቸው እንደ ፓሪስ የአየር ንብረት ለውጥ ስምምነት፤ እ.ኤ.አ. እስከ 2030 የሚተገበረው የዘላቂ የልማት ግቦች አጀንዳ እና እ.ኤ.አ. እስከ 2063 የሚተገበረው የአፍሪካ አጀንዳዎችን በገባነው ቃል መሠረት ለመፈፀምም የሚረዳ ፕሮግራም ነው።

የብሄራዊ አረንጓዴ ልማትና የችግኝ ተከላ ስልታዊ እርምጃ በግብታዊነት የተጀመረና የሚሰራ ሳይሆን ቀደም ብሎና አሁንም ተቀርፀው በተግባር ላይ የሚገኙ የፖሊሲ፣ የፕሮግራምና የስትራተጂ ሰነዶች ታግዞ የሚመራና የሚተገበር ነው። ከዚህ ረገድ እ.ኤ.አ. በ2011 በደርባን ደቡብ አፍሪካ በተካሄደው የተ.መ.ድ. የአየር ንብረት ለውጥ ጉባኤ ላይ ለዓለማቀፉ ማህበረሰብ ኢትዮጵያ ይፋ ያደረገችውና ላለፉት አስር አመታት በስራ ላይ ያለው "ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ልማት ስልት (CRGE)፣ የደን ዘርፍ ትራንስፎርሜሽን ፕሮግራም፣ የሬድ+ ሰለት እና ብሄራዊ የቀርከሀ ልማት ስልትና መርሀ ግብር ተጠቃሽ ናቸው። በተጨማሪም እነዚህ ፕሮግራሞች እና ስልቶች ከዓለማቀፍ የዘርፉ የልማት ግቦች ጋር የተጣጣሙና የኢትዮጵያን የደን ልማት፣ የተራቆቱ መሬቶች መልሶ በደን የመሸፈን ፍላጎትና ጥረት፣ ከተሞችን የማደስና አረንጓዴ የማድረግ እና የደን ጥበቃና ዘላቂ አጠቃቀምን በቀጣይ አስር አመታት እውን ለማድረግ ታስቦ እየተከናወኑ ይገኛሉ።

የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ልማት ስልት በደን ልማትና ጥበቃ ብቻ ያልታጠረና ዘርፍ ዘለል የሆኑና በርካታ ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸው ውጤቶችን አጣጥሞ የሚያሳካ ነው። በሰብል ምርት የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ይቻል ዘንድ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተጣጣመ የአመራረት ዘይቤን ማስፋፋት፣ የኋይል ምንጫችንን ከታዳሽ ኋይሎች ማምረት፣ መጠቀምና የበካይ ጋዞችን ልቀት መቀነስ በስልቱ ትኩረት የተሰጣቸው አበይት ጉዳዮች ናቸው። ታዳሽ ኋይልን ከመጠቀም አንፃር በሀገራችን ከተተገበሩ ተግባራት ውስጥ ማሳያ ለመጥቀስ ያህልም:-

- የኢትዮጵያ ወቅታዊ የሀይል ፍላጎት ማሟያ አማራጭ 97% ከታዳሽ ሀይል መሆኑ፤
- እ.ኤ.አ. በ2025 እውን የሚሆነውና "ብርሀን ለሁሉም" በሚል መሪ ሀሳብ የኤሌትሪክ ሀይል ለሁሉም የሀገራችን ህዝቦች በመስመርና በመስመር አልባ አማራጮች ለማዳረስ ታቅዶ እየተሠራ ያለው ከታዳሽ ኋይል ነው፡፡ በሀገራችን 2400 ቶን ያህል የሚሆን በካይ ጋስ ምንጩ ዜጎች ምግባቸውን ለማብሰል እና ብርሀን ለማግኘት (ኩራዝ) ከሚጠቀሙባቸው ታዳሽ ያልሆኑ የሀይል ምንጮች ነው። ይህም ተጠቃሚ የአጠቃላይ ህዝቡን ወደ 56% ያህል ይሸፍናል። ይህ ማለት ደግሞ በዚህ ችግር ብቻ የከባቢ አየር ሙቀት በ2.2 ሚሊዮን ቶን የተቃጠለ በካይ አየር ($Co_2e$) ይባባሳል። ከታዳሽ ኋይሎች የተገኘ በቂ የኤሌክትሪክ ሀይል ለማብሰያና ለመብራት ባለመኖሩ የበዛ የደን ጭፍጨፋ፣ የመሬት መንሳት እና መሸርሸር፣ እንዲሁም የጠቃሚ ማዕድናትን ከእርሻ መሬቶች መቀነስን ያስከትላል።
- በቅርቡ ተከልሶ ወደስራ የገባው "ብሄራዊ የኤሌክትሪክ ሀይል ለዜጎች ማዳረስ ፕሮግራም" አሁን ያለውን 44% የኤሌክትሪክ ሀይል ተደራሽነት ሽፋን ታዳሽ ሀይልን ብቻ በመጠቀም እ.ኤ.አ. በ2025 100% ለማድረስ ያለመ ነው።

ሌሎች የካርበን ልቀትን ለመቀነስ ታልሞ ከተቀረጹ የልማት ስልቶች ውስጥ "ሽገርን የማስዋብ" ፕሮግራም፣ የአዲስ አበባ ከተማ የቀላል ባቡር ትራንስፖርት ስርዐት፣ በአፍሪካ የመጀመሪያው ኢትዮጵያንና ጅቡቲን የሚያገናኘው የኤሌክትሪክ ባቡር ትራንስፖርት ስርዐት እና ጅቡቲና ሱዳን ከበካይ ጋዞች የሚያመርቱትን ሀይል እንዲተኩ ከኢትዮጵያ የሚቀርብላቸው የታዳሽ ኋይል ይገኙበታል፡፡

ከዚህም በመነሳት የኢትዮጵያ መንግስት በራሱና በልማት አጋሮች ድጋፍ እ.ኤ.አ. በ2030 ለማሳካት የታቀደውን የዘላቂ የልማት ግቦች ትልም ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ በትክክለኛ መስመርና ሁኔታ ላይ መሆኑን በልበ ሙሉነት መናገር ይቻላል።

**የ2012 በጀት ዓመት ብሄራዊ የአረንጓዴ ልማት መርሀ ግብር፤ የዕቅዱ አፈፃፀምና ያጋጠሙ ተግዳሮቶች**

ከላይ እንደተገለፀው ኢትዮጵያ የዓየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለመቋቋም በርካታ ስልቶችን ቀርፃ በመተግበር ላይ ትገኛለች፡፡ የደን ጭፍጨፋን መቀነስ፤ የአፈር መከላትን መቆጣጠር፤ የውሀ ሀብት ብክነትን ማሻሻል፤ የበካይ ጋዞች ልቀትን መቀነስና የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ በዚህ ረገድ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

ለዚህም ነው የአረንጓዴ አሻራ መርሀ ግብር ተቀርፆ በመተግበር ላይ የሚገኘው፡፡ ይህንን ጥረት ወደላቀ ደረጃ ለማድረስ ይቻል ዘንድ መንግስት ባለፈው በጀት ዓመት ከ2012-2015 ድረስ 20 ቢሊዮን ችግኞችን በመላ ሀገሪቱ የመትከል ትልሙን ይፋ አድርጓል፡፡ የሚከተሉት ሰንጠረዦች የ2012 በጀት ዓመት የችግኝ ተከላ መርሀ ግብር ዕቅድና አፈፃፀም እንዲሁም የክልሎች የአፈፃፀም ስርጭትን ያሳያሉ፡፡

ከገፅ ፫ የቀጠለ...

| | በበጀት ዓመቱ በተለያዩ ባለድርሻዎች ችግኝ ያፈሉ ጣቢያዎች (2012) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ክልል** | **በመንግስት** | **በመ.ያ.ዶች** | **ፕሮጀክቶች** | **በማህበረሰብ** | **አጠቃላይ** |
| አማራ | 3,327 | 0 | 118 | 4,448 | 7,893 |
| ደብብህ | 4,765 | 182 | 241 | 886 | 6,074 |
| ኦሮሚያ | 1,501 | 79 | 182 | 8,401 | 10,163 |
| ትግራይ | 237 | 0 | 34 | 71 | 342 |
| **አጠቃላይ** | **9,830** | **261** | **575** | **13,806** | **24,472** |

**ሰንጠረዥ 1. በኦሮሚያ፣ አማራ፣ ትግራይና ደብብህ ክልሎች የተፈሉ ችግኞች ቁጥር (2012)**

| **በ2012 ለተከላ የተዘጋጁ ችግኞች ብዛት (በሚሊዮን)** | | | | | **በ2012 በጀት ዐመት የተተከሉ ችግኞች ብዛት (በሚሊዮን)** | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ክልል** | **ዛፎች** | **የጥምር ግብርና ዝርያዎች** | **የከተማ ዛፎች** | **አጠቃላይ** | **ዛፎች** | **የጥምር ግብርና ዝርያዎች** | **የከተማ ዛፎች** | **አጠቃላይ** |
| አዲስ አበባ | - | - | 6 | 6 | | | 7.88 | 7.88 |
| አፋር | 2 | 3 | 1 | 6 | 2.36 | 0.895 | 0 | 3.255 |
| አማራ | 1,030 | 380 | 4 | 1,414 | 1072.99 | 422.25 | 18.2 | 1513.44 |
| ቤኒሻንጉል ጉምዝ | 14 | 7 | 1 | 22 | 14.36 | 10.74 | 1.67 | 26.77 |
| ድሬደዋ | - | - | 1 | 1 | | 0.334 | 0.533 | 0.867 |
| ጋምቤላ | 1 | 2 | 1 | 4 | 1.29 | 0.43 | 0.08 | 1.8 |
| ሀረሪ | 1 | 1 | - | 2 | 0.04 | | 1.77 | 1.81 |
| ኦሮሚያ | 1,260 | 1,340 | 10 | 2,610 | 1209.9 | 851.27 | 52.6 | 2113.77 |
| ደብብህ | 251 | 580 | 5 | 836 | 917 | 554 | 27.11 | 1498.11 |
| ሶማሌ | - | 1 | 1 | 2 | 1.12 | 0.37 | 0 | 1.49 |
| ትግራይ | 83 | 12 | 2 | 97 | 55.55 | 8.31 | 0 | 63.86 |
| **አጠቃላይ** | **2,642** | **2,326** | **32** | 5,000 | **3,274.61** | **1,848.60** | **109.84** | **5,233.052** |

**ሰንጠረዥ 2. በየክልሎች የፈሉና የተተከሉ ችግኞች ብዛት ቁጥር (2012)**

ካለፈው ዓመት ተሞክሮና ገጠመኝ ልምድ በመውሰድ በ2012 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራን ስራ ለማከናወን የክልል መንግስታትና ሶስቱ ስራውን በበላይነት እንዲያስተባብሩ ሀላፊነት የተጣለባቸው ተቋማት ማለትም የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን፣ የግብርናና ተፈጥሮ ሀብት እና የውሀ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስትሮች አስቀድመው በቂ በጀት በመመደብ በቂ ዝግጅት አድረገዋል፡፡ በግልፅ ለማሳየት ያህልም የግብርናና ሚኒስቴር 183.1 ሚሊ. ብር፤ የውሀ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር 83.2 ሚሊ. ብር እና የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን 74.5 ሚሊዮን ብር፤ በአጠቃላይ 340.8 ሚሊዮን ብር ለበጀት ዓመቱ የችግኝ ተከላ አውጥተዋል፡፡

**በሂደቱ ያጋጠሙ ተግዳሮቶች**

እንደሚታወቀው ባለፈው ዓመት የተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ዓለማቀፋዊ ተግዳሮት ሆኖ ቆይቷል፤ አሁንም ሆኖ ቀጥሏል፡፡ ይሁንና ኢትዮጵያ ተግዳሮቱን ለቋቋምና ለመከላከል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እስከማወጅ የዘለቀ በርካታ እርምጃዎችን ወስዳለች፡፡

ብሄራዊ የችግኝ ተከላ መርሀ ግብሩም "ራሳችንን ከኮሮና ቫይረስ እየተከላከልን ችግኝ እንተክላለን" በሚል መሪ ሀሳብና የጤና ጥበቃ ምክር እና የመከላከያ መመሪያዎች በተከተለ አሰራር ተከናውኗል። በዚህም መሰረት በሀምሌና ነሀሴ የክረምት ወራት የ 5 ቢሊዮን ችግኞች ተከላ ዕቅዱን ከተቀመጠው ዒላማ በላይ ከአርሶ አደሮችና ከግል ተቋማት ችግኞችን በተጨማሪ በመግዛት ማሳካት ተችሏል፡፡

## ሁነቶች

ዓለማቀፉን የኮሮና ወረርሽኝ መከሰት ተከትሎ በርካታ አካባቢ ነክና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ አልመው የታቀዱ ሁነቶች ተራዝመዋል፣ ተሰርዘዋልም፡፡ ይሁንና ክፍተቱን ለመሙላት የተለያዩ ምክክሮችና ትብብሮች የቀጠሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል የሚከተሉት ሁነቶች በበይነ መረብ አማካይነት ይከናወናሉ፡፡ እነዚህ ሁነቶች ለተሳታፊዎች ክፍት የሆኑ ሲሆን እያንዳንዱን ሁነቶች በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት ካስፈለገዎ የማስፈንጠሪያ ቁልፉን በመጫን ማግኘት ይችላሉ፡፡

- የከተማ ነጋዊ ሁኔታዎች ጉባኤ፣ ዓለማቀፍ የኢንዱስትሪ፣ አካባቢያዊና የንዋይ ጥናት ማዕከል፣ እ.ኤ.አ. ኦክቶበር 2020 | ምንጭ
- የ2020 ውጤታማ ከተሞች፣ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን አስመልክቶ ከተሞችን ለሚያስተዳድሩ መሪዎች በበይነ መረብ የተዘጋጀ ዓለማቀፍ ጉባኤ፣ በ ICLEI እና የፌደራላዊ ቦን ከተማ ግዛት ትብብር የተዘጋጀ፤ እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 2020 | ምንጭ
- የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅኖዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን በኢትዮጵያ፣ ጋና፣ ኬንያና ደቡብ አፍሪካ ለሚገኙ በሀብት ላይ ለሚወስኑ የፋይናንስ ዘርፍ አመራሮች፣ CDKN፣ እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 2020 | ምንጭ
- የሽግግር ጊዜ፤ የዓለማቀፍ የልማት ግቦችን አፋጥኖ ለማሳካት የሚያስችሉ ወቅታዊ የትብብር ስልቶች እና አቅጣጫቸው፣ WRI፣ እ.ኤ.አ. በኦክቶበር 2020 | ምንጭ
- ሲቪል ማህበራት እና ለአስጊ የዐየር ሁኔታ ለውጥ ዝግጁነት፣ ክላይ**ሜ**ት አውትሪች፤ እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 2020 | ምንጭ
- እ.ኤ.አ. የ2020 የአረንጓዴ እድገት እና የዘላቂ ልማት ፎረም፣ ኦ.ኢ.ሲ.ዲ.፤ እ.ኤ.አ. ኖቬምበር 2020 | ምንጭ
- የኢንተርኔት ስልጠና-የግሉ ዘርፍና የመንግስት ቁርኝት-የመስኖ ልማት ውጤታማነት ማሻሻያ ስልቶች (በግል ጊዜ የሚወሰን) እ.ኤ.አ. በ31 ዲሴምበር 2020 | ምንጭ
- የኢንተርኔት ስልጠና፤ ዝቅተኛ የካርቦን ልቀትን እውን ለማድረግ የፖሊሲ ሚና፤ ከዕቅድ እስከ ትግበራ (በግል ጊዜና ፍጥነት) እ.ኤ.አ. በ31 ዲሴምበር 2020 | ምንጭ
- የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ጉባኤ እ.ኤ.አ. ጃንዋሪ 2021 | ምንጭ

## ትኩረት ለፆታ ተኮር የአየር ንብረት እንቅስቃሴ

- ***በ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ አስተግባሪ (ፋሲሊቲ) የተዘጋጀ***

የኢትዮጵያ መንግስት እ.ኤ.አ. ከ2011 ጀምሮ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስልትን በመቀየስና በመተግበር ሁሉን አቀፍ የሆነ የኢኮኖሚ እድገት ከተለዋዋጭ የአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተጣጣመ ሁኔታ ሲያስመዘግብ ቆይቷል፡፡ ለዚህም ስልት ተግባራዊነት ኢትዮጵያ ሀገር አቀፍ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ማጣጣሚያ ዕቅድ (NAP) አዘጋጅታለች፣ ስልቱን የሚተገብሩ የዘርፍ ሚኒስቴር መ/ቤቶች በሚመለከታቸው መልኩ ዕቅዱን የዕቅዳቸው አካል አድርገዋል፤ የስራውን ተግባራዊነት የሚያስተባብርና የሚያስተገብርም ራሱን የቻለ የስራ ክፍል (CRGE Facility) ተቋቁሟል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ለአየር ንብረት ለውጥ ቅነሳ ያላትን ቁርጠኝነት በተግባር በማሳየት በዓለማቀፍ ደረጃ ከተቀመጠው የጊዜ መርሀ ግብር ቀድማ "በፈቃደኛነት ላይ የተመሠረተ የአየር ንብረት አሉታዊ ተፅኖዎች እቅድን (iNDC) በማዘጋጀት ለሚመለከተው አካል አስገብታለች። ለስልቱና ለዕቅዶቹ ተግባራዊ መሆንም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የሚጣጣሙ የተለያዩ ፕሮግራሞችን በመቅረፅ በሁለት አካላት ትብብር ማለትም በገንዘብ ሚኒስቴር እና በአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን የሚመራው አስተባባሪ ክፍል ወደ ትግበራ ገብቷል፡፡

የኢትዮጵያ ህገ መንግስት የፆታ እኩልነትን በግልፅ ይደነግጋል፡፡ ህገ መንግስታዊ ድንጋጌውን እውን የሚያደርጉ ፖሊሲዎችም ተቀርፀው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡ ከዚህ አኳያ ብሄራዊ የሴቶች ፖሊሲ እና ብሄራዊ የሴቶች የልማት መርሀ ግብር ለፆታዊ እኩልነት የሚሉ ሰነዶች ተጠቃሽ ናቸው፡፡ ፖሊሲዎቹን ወደ ተግባር የሚያስፈፅምና ከፌደራል እስከ ቀበሌ የተዋቀረውና ቀደም ብሎ "የሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር" ተብሎ የሚጠራውና በቅርቡ መሰረተ ሰፊ በሆነ ሁኔታ "የሴቶች፣ ህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር" በሚል የተዋቀረው ሚኒስቴር መስሪያ ቤት እ.ኤ.አ. ከ2005 ጀምሮ በስራ ላይ ያገኛል፡፡ ከተቋቋመ አንስቶም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ከተለያዩ ባለድርሻዎች ጋር በመሆን በሀገሪቷ የፆታ እኩልነትን የሚያረጋግጡ በርካታ ፕሮግራሞችን ቀርፆ በመተግበር ተጨባጭ ለውጦችን አስመዝግቧል፡፡

በበርካታ ጥናቶች እንደተረጋገጠው የአየር ንብረት ለውጥ አሉታዊ ተፅኖ ይበልጥ ተጎጂ የሚያደርገው በተለያዩ ምክንያቶች ከማህበረሰቡ የተገለሉና አድሎ በሚፈፀምባቸው የማህበረሰብ ክፍሎች ላይ ነው፡፡ በመሆኑም የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለመቋቋም የሚሰሩ ስልታዊ ስራዎች እነዚህን የማህበረሰብ ክፍሎች ያማከሉና ተጠቃሚ የሚያደርጉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዓለማችን በድህነት ወለል ላይ ከሚኖሩ የማህበረብ ክፍሎች ውስጥ አብዛኞዎቹ ሴቶች መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ሴቶች በአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ ይበልጥ ተጋላጭና ተጎጂዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ሴቶች የአየር ንብረት ለውጡን የመቋቋም አቅማቸው በሌሎች ጎጂ ልማዳዊ አስተሳሰቦች ማለትም የመሬት ሀብት ይዞታ አለማግኘት፣ ሌሎች ንብረቶችን የማፍራትና የመጠቀም ተፅኖዎችና በውሳኔ ሰጪነት ያላቸው ሚና አናሳ መሆን ይበልጥ ተጎጂ ያደርጓቸዋል፡፡ እነዚህንና መሰል በርካታ ችግሮች ለመቅረፍ ይረዳ ዘንድና የሴቶችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የፆታዊ ትንተና፣ የአፈፃፀም መመሪያዎችና

# ኤን.ዲ.ሲ. ሀይላይትስ

ቅፅ ፩፣ቁጥር ፪

## ልዩ ልዩ ህትመቶች

### የአቅም ግንባታ የኪስ ማስታወሻ




አካባቢያዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የተለያዩ የአቅም ግንባታ ስራዎችን የሚያከናውነው ኢንስቲትዩት (ECBI) በዘርፉ የሚከናወኑ የአቅም መገንቢያ ስራዎች የሚመሩበት የኪስ ማስታወሻን በቅርቡ ከልሶ ይፋ አድርጓል። የማጣቀሻ መመሪያው የተለየ አፅንኦት የሰጠው በተ.መ.ድ የአየር ንብረት ለውጥ ማዕቀፋዊ ስምምነት አሰራር፣ ደረጃና ማዕቀፍ መሰረት የአቅም ግንባታ ስራዎች በምን ሁኔታ እንደሚከናወኑና አለም አቀፍ ጥረቶች እንዴት መሻሻል እንደሚኖርባቸው ነው፡፡ምንጭ

### የብዝሀ ህይወት ሚና፡ ለምግብ ዋስትናና ለስርዐተ ምህዳር ጥበቃ




የአለም የእርሻና ምግብ ድርጅት ባካሄደው ጥናት ለምግብ እና እርሻ ምርት ማሳደግ የምናውለው የብዝሀ ህይወት ልማትና ጥበቃ ለዘላቂ የስርዐት ምዳር ጥበቃ ጉልህ ሚና እንዳለው ይፋ አድርጓል፡፡ ምንጭ

### "የሊቪንግ ፕላኔት" የ2012 ዘገባ




WWF የተሰኘውና ሊቪንግ ፕላኔት በሚል ስያሜ በየአመቱ ጥናታዊ ዘገባዎችን የሚያወጣው ተቋም እ.ኤ.አ. በ2020 ዘገባው አጽንኦት ሰጥቶ እንዳስነበበው የሰው ልጆች በተፈጥሮ ላይ በማድረስ ላይ የሚገኙት ገደብ አልባ ጥፋት በዱር እንስሳትና በሰው ልጆች ጤናና የአኗኗር ዘይቤ ላይ አደጋ ጋርጧል፡፡ ምንጭ

**ከገፅ ፫ የቀጠለ...**

የአተገባበር መረጃዎች በአግባቡ ተጠንተውና ተተንትነው በሀገራዊ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልትና በብሄራዊ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ዕቅድ ውስጥ ተካተው በመተግበር ላይ ይገኛሉ፡፡

ይሁንና በተደጋጋሚ በሚከናወኑ የአተገባበር ግምገማ ሪፖርቶች መገንዘብ እንደተቻለው የሴቶችን ተጠቃሚነት በዘርፉ ለማረጋገጥ የወጡ ፖሊሲዎችንና ፕሮግራሞችን በማከናወን ረገድ ክፍተቶች መኖራቸው ተስተውሏል፡፡ በዚሁ መነሻነት የሴቶችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ስራዎችን በሁሉም ዘርፎችና መዋቅሮች ለማረጋገጥ የልማት ስልቱን የሚያስተባብረው አካል "ዓለማቀፍ የአረንጓዴ ልማት ኢንስቲትዩት (GGGI)" ከተባለ አጋር ድርጅት ጋር በመተባበር የሴቶችን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ፆታ ተኮር ማዕቀፍ (gender framework) ቀርጿል፡፡ የዚህ ማዕቀፍ ዓላማም ፆታ ተኮር ጉዳዮች በሀገሪቱ እየተተገበረ ባለው ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ልማት ስልት ጋር ተጣጥሞ እንደተካተተና በየደረጃው በሚገኙ የስልቱ ተግባሪ ቁልፍ ባለድርሻ አካላት የጋራ ግንዛቤና መግባባት እንደተደረሰበት መፈተሽ ነው።

በቅርቡ ፆታዊ እኩልነትና ፆታ ነክ ጉዳዮችን አስመልከቶ የተደረገ ጥናት ውጤት እንዳመላከተው በሁሉም የከፍተኛ የመንግስት መዋቅር አካላትና አመራሮች ዘንድ ከፍተኛ ግንዛቤና የመፈፀም ቁርጠኝነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ በእያንዳንዱ ሚኒስቴርና ሚኒስቴር ያልሆኑ የመንግስት አስፈፃሚ አካላት ውስጥም የሴቶችን ጉዳይ የሚሰራና የሚከታተል "የሴቶች ጉዳይ የስራ ክፍል" ተደራጅቶ ይገኛል፡፡ ይሁንና የሴቶችን እኩልነት የሚያረጋግጡ ስራዎችን በየተቋማት አካቶ ከማቀድና ከመተግበር አኳያ ክፍተቶች ታይተዋል፡፡ ከተቋማት ዘርፍ ተኮር ፖሊሲዎችና ዕቅዶ ውስጥ በተለይ የአየር ንበረት ለውጥ በሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ተፅኖ ለመቀነስ የተቀመጡ ሀገራዊ ትልሞችን በዕቅዳቸው ከማካተትና ከመተግበር ረገድ ጎላ ያለ ክፍተት አለ፡፡ የዚህም ክፍተት ዋና መንስኤ ዘርፎች የፖሊሲና ዕቅዶቻቸውን በሚቀርፁበት ጊዜ በቂ የሆነ የፆታዊ ትንተና አለማድረጋቸውና በየተቋማት የሴቶችን ጉዳዮች እንዲያስተባብሩና እንዲያስተገብሩ የተቀመጡ የስራ ክፍሎችን በበቂ ሁኔታ ያለማሳተፍ ነው፡፡

በተለያዩ አካላትና ደረጃዎች የሚስተዋሉ የአፈፃፀም ጉለቶች እንደተጠበቁ ሆነው የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስልታዊ ሰነድና ሰነዱን ለማስተግበር የተቀረፁ ፕሮግራሞችና ዕቅዶች የሴቶች ጉዳይ በተቻለ መጠን ተካቶና ተተግብሮ ሴቶችን ተጠቃሚ እንዲያደርግ በሀገር አቀፍ ደረጃ ስራውን የሚያስተባብሩ አካላት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ እንደ አብነትም የፆታ ትንተና ተሰርቷል፣ ፆታ ተኮር ጉዳዮችን በየዘርፉ ዕቅድ ለማካተት የሚረዳ ስልት ተጠንቶ ተሰራጭቷል፣ ለኢትዮጵያ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ

**ከገፅ ፮ የቀጠለ...**

ማጣጣሚያ ዕቅድ ተጠንቷል፤ የፆታዊ ጉዳዮች በሰነዶች መሰረት መተግበራቸውን የሚቆጣጠርና የሚከታተል ባለሙያ ተቀጥሯል፤ የአተገባበር መመሪያዎች፣ ቅፆችና መሰል ሰነዶች በሙሉ ተዘጋጅተው ለሚመለከታቸው አካላት ስልጠና በመስጠት ጭምር ተሰራጭተዋል፤ ክትትልና ድጋፍም ይደረጋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት እንቅስቃሴዎች ያሉ ክፍተቶችን የሚያመላክቱ በመሆኑ በጣም ወሳኝነት አላቸው፡፡ ለምሳሌ የአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ዕቅድ ሰነድ ላይ የተሰራውን የፆታ ትንተና ጥናት (NAP gender analysis) ካመላከተው ክፍተቶች መካከል፤ በአየር ንብረት ለውጥ ማጣጣሚያ ስራዎች ላይ የሚስተዋለው  የፆታ የፍላጎት፣ የተጠቃሚነት እና የመተግበር አቅም ልዩነት፤ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለማጣጣም የሚከናወኑ ስራዎችን በሚመለከት በእኩልነት መሳተፍ፣ የሚተገበረው ስራ ምርጫን አስመልክቶ ግፊት ማድረግና መወሰን መቻል፤ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖን ለማጣጣም በሚመደብ ሀብት አጠቃቀምና አስተዳደር ላይ እኩል ተሳታፊና ወሳኝ መሆን ይገኙበታል፡፡ (እንግሊዝኛው እንዲ ለማለት መሰለኝ)

እ.ኤ.አ. በዲሴምበር 2019 ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ግንባታ ስልትን በሀገር ደረጃ የሚያስተባብረው (CRGE ፋስሊቲ) ባዘጋጀውና በሀገሪቱ የሚገኙ ቁልፍ የስርዐተ ፆታና የአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚሰሩ ባለድርሻዎች በተሳተፉበት የሁለት ቀናት ምክክር መድረክ ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የኢኮኖሚ ልማት ስልት ውስጥ የተካተቱ ጉዳዮችን አስመልከቶ የአተገባበር ሪፖርት ቀርቦ ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በዚህ የምክክር መድረክ ላይ የአተገባበር ሪፖርት ግኝቶች ላይ በማተኮር በገንዘብ ሚኒስቴር፤ በአካባቢ፣ በደን እና አየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽን እንዲሁም በሌሎች ተግባሪ የዘርፍ መስሪያ ቤቶች  የታዩ ጉለቶችና የተመዘገቡ ውጤቶች ተገምግመዋል፡፡ ከውይይቱም በመነሳት ተሳታፊዎች እስካሁን በተከናወኑና በቀጣይ መከናወን በሚገባቸው ስራዎች ላይ ሰፋፊ ግብዐቶችንና አስተያየቶችን የሰጡ ሲሆን የሚከተሉት ምክረ ሀሳቦችም በመድረኩ ላይ ቀርበዋል፡-

- **ስርዐተ ፆታን የተመለከቱ ጉዳዮችን በአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቋቋም ስራዎች ውስጥ ስለማካተት**፡- ስልቱን በሚተገብሩ አስፈፃሚ መ/ቤቶች ውስጥ የሚዘጋጁ የዘርፍ ፖሊሲዎችና ዕቅዶች በሚዘጋጁበት ወቅት የፆታዊ ትንተና ጥናት እንዲከናወንና ስርዐተ ፆታና የአየር ንብረት ለውጥ (ተፅኖ) የሚኖራቸው ቁርኝትም በሁሉም ተቋማት በሚገባ ሊተነተንና ሊካተት ይገባል።

- **ፆታ ተኮር የበጀት አመዳደብ ስርዐት**፡- ስርዐተ ፆታን በአየር ንብረት ለውጥ ተጋላጭነት ቅነሳ እቅድ ውስጥ ማካተት ማለት የስርዐተ ፆታ ትንተና ለመስራት በቂ ሀብት መመደብን፣ ፆታ ተኮር ጉዳዮችን በአግባቡ መተግበርን እና በቂ የክትትልና ድጋፍ ስራዎች መስራት ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም በገንዘብ ሚኒስቴር የተዘጋጀውን የፆታ ተኮር በጀት መመሪያን በበቂ ሁኔታ ማስተዋወቅ ይገባል።

- **አካባቢያዊና ማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲ፡-** የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲዎች መኖርና መጠናከር ስርዐተ ፆታን አማክሎ ለመተግበር ምቹ መንደርደሪ ነው፡፡ በመሆኑም የአካባቢያዊና ማህበራዊ ደህንንትና ጥበቃ ስራዎች እግረ መንገዳቸውን የስርዐተ ፆታን ተግባራዊነት ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

- **አቅም ግንባታና ድጋፍ**፡- በዘርፉ የሚስተዋለውን የአተገባበር ክፍተት ለመሙላት የአቅም ግንባታ ስራዎች የስርዓተ ጾታ እና የዓየር ንብረት ለውጥ መመሪያዎችና የአሰራር ዘደ፞ዎች ላይ ብቻ ማተኮር የለባቸውም፡፡ ይልቁንም የስርዓተ ጾታ ትንተና፣ የስርዓተ ጾታ መርሀ ግብሮች እና የክትትል፣ ድጋፍና ግምገማ አሰራሮችን ማካተት ያስፈልጋል፡፡

- **የትብብርና መደጋገፍ ስርዐት መኖር፡-** በምክክር መድረኩ ከሁሉም ተግባሪ የዘርፍ መስሪያ ቤቶች በተወከሉ አባላት የተዋቀረና ስራውን የሚያስተባብር አንድ ቡድን የመቋቋምን አስፈላጊነትና እርስ በርስ መደጋገፍ የሚያስችል ስርዐትንም መዘርጋት እንደሚገባ ሀሳብ ቀርቧል፡፡ ይህ መኖሩ በግንዛቤ ፈጠራ፣ በዘርፍ የፖሊሲና ፕሮግራሞች ቀረፃ የስርዐተ ፆታና የአየር ንብረት ለውጥ ጉዳዮች መካተትን ለማረጋገጥና በሁሉም የተቀዋማት የመዋቅር እርከኖች ስራው በተመሳሳይ ሁኔታ እንዲተገበር ይረዳል ተብሏል፡፡

እነዚህን ግብዐቶች በመውሰድ የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ኮሚሽንና የገንዘብ ሚኒስቴር  የአረንጓዴ ልማት ስልት ትግበራ አስተባባሪዎች እና የየተቋማቱ የስርዐተ ፆታ የስራ ክፍሎች የዕቅዳቸው አካል በማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማከናወን ለግብዐቶቹ እውን መሆን ይሰራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በውይይቱ ወቅት የተሰጡ ግብዐቶች በቀጣይ የሀገራችንን በፈቃደኛነት ላይ የተመሰረተ የአየር ንብረት ለውጥ ተፅኖ መቀነሻ ዕቅድ ሲከለስ እንደ ግብዐት ለማካተት ዕድል የሚሰጡ ጠቃሚ ግብዐቶች ናቸው።

